# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ.209896

ሐምሌ 5 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካቾች፡.....1. ወ/ሮ ጀማነሽ ቱፋ ዱጉማ

2. ወ/ሪት ረድኤት ሰይፉ መንግስቱ } የቀረበ የለም

3. ወ/ሪት ኤደን ሰይፉ መንግስቱ }

ተጠሪ፡.....ወ/ሮ ሶፊያ ከበደ ቀርቧል

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍርድ

ይህ የዉርስ ሀብት ይጣራልን ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካቾች የሥር አመልካቾች፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ጣልቃ ገብ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካቾች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.186518 መጋቢት 30 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ የ1ኛ አመልካች ባለቤት እና የ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ወላጅ አባት አቶ ሰይፉ መንግስቱ ነሸ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ በመሆናቸዉ፣ 1ኛ አመልካች ሚስት እና 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ልጆች ወራሽነታቸዉን አረጋግጧል፡፡ 1ኛ አመልካች እና ሟች በጋራ ንብረቶችን አፍርተናል፡፡

ማ ሰታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በመሆኑም የዉርስ ሀብቱ ተጣርቶ የ1ኛ አመልካች የሚስትነት ድርሻ እና የ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የወራሽነት ድርሻቻዉን እንዲንካፈሉ እንዲወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡

ፍ/ቤቱም ሟች የዉርስ ሀብት ተጣርቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ በመስጠት በመጠባበቅ ላይ እያለ፣ ጣልቃ ገብ (የአሁን ተጠሪ) ባቀረቡት አቤቱታ ጣልቃ ገብ የሟች ሚስት መሆኔን በፍ/ቤት ያረጋገጥኩኝ ስለሆነ በዚህ ክርክር ጣልቃ ገብቼ እንዲከራከር እንዲፈቀድልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ፍ/ቤቱም የጣልቃ ገብ አቤቱታን በመቀበል በክርክሩ ገብተዉ እንዲከራከሩ ፈቅዷል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የዉርስ አጣሪ ባቀረበዉ ሪፖርት ላይ የግራ ቀኙን አስተያየት በመቀበል በመመርመር ባሳለፈዉ በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 04 ዉስጥ የሚገኘዉ የቤት ቁጥር 860 የሆነዉን የመኖሪያ ቤት በሟች ስም የተመዘገብ ሲሆን ግማሹ የ1ኛ አመልካች ድርሻ እና ግማሹ ደግሞ የ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የሁለቱ ወራሾች እኩል እንዲካፈሉ እና ከዉርስ ሀብት የሚከፈል እዳን በተመለከተ በዉርስ ሪፖርቱ ላይ የተጠቀሰዉን በመቀበል አጽድቋል፡፡ በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር B07 እና 08 የሆነዉ ድርጅት በጣልቃ ገብ ስም የተመዘገበ ሲሆን ግማሹ (50%) የጣልቃ ገብ ድርሻ፣ ቀሪዉ ግማሽ (50%) የሟች አቶ ሰይፉ መንግስቱ ድርሻ የወራሾች የ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች እና የ1ኛ አመልካች ድርሻ በአጠቃላይ ከቤቱ 1/4ኛ ድርሻ አላቸዉ በማለት ሪፖርቱን በማሻሻል ወስኗል፡፡ በን/ስ/ላ/ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ዉስጥ የሚገኘዉ የቤት ቁጥር አዲስ፣ የሰሌዳ ቁጥር 02-01-29047 አ.አ. አዉቶሞቢል መኪና፣ በተለያዩ ባንኮች አለ የተባለዉን ተቀማጭ ገንዘብ እና በአዲስ ኢንተርናሽናል አ.ማ አለ የተባለዉን የአክስዮን ድርሻ እና ትርፍ 1ኛ አመልካች፣ ጣልቃ ገብ እንዲሁም የሟች ወራሾች እኩል ልካፈሉ ስለሚገባ ለ1ኛ አመልካች 1/3ኛ፣ ለጣልቃ ገብ 1/3ኛ እንዲሁም ለ2ኛ እና ለ3ኛ አመልካቾች የአባታቸዉን ድርሻ 1/3ኛ ይገባቸዋል በማለት የዉርስ አጣሪ ሪፖርቱን በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካቾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር ባሳለፈዉ ዉሳኔ በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 09 ክልል ዉስጥ የሚገኘዉ የቤት ቁጥር B07 እና 08 የሆነዉ ድርጅት ቤት በጣልቃ ገብ ስም የተመዘገበ ቢሆንም ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክርም ሆነ ባቀረቡት ማስረጃ በንብረቱ ላይ በተለየ መንገድ ጉልህ የሆነ አስተዋጽኦ ስለማድረግ በማስረጃ ያረጋገጡት ጉዳይ ባለመሆኑ፣ ይህን ቤት በተመለከተ የሟች ድርሻ 50% ለሕጋዊ ወራሾች ለ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች እኩል ድርሻቸዉን እንዲካፈሉ፤ ቀሪዉን 50% ድርሻ ደግሞ 1ኛ አመልካች እና ጣልቃ ገብ እኩል እያንዳንዳቸዉ 25% ሊካፈሉ ይገባል በማለት የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በዚህ ረገድ በማሻሻል፣ በሌሎች ጉዳዮች ቀሪዉን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ክፍል በማጽናት ወስኗል፡፡

ጣልቃ ገብ (የአሁን ተጠሪ) በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር ባሳለፈዉ ዉሳኔ 1ኛ አመልካች እና ጣልቃ ገብ የሟች ሕጋዊ ሚስቶች መሆናቸዉ፤ አከራካሪዉ በኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 09 ዉስጥ የሚገኘዉ የቤት ቁጥር B07 እና 08 የሆነዉ ድርጅት ቤት በጣልቃ ገብ ስም የተመዘገበ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ስለሆነ፣ የ1ኛ አመልካች ክርክር ከዚህ ቤት 1/4ኛ ድርሻ ይገባኛል

ስለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፤ 1ኛ አመልካች ይህ ንብረት ሲፈራ ለ30 ዓመታት አሜሪካን አገር የኖሩና አሁንም እየኖሩ የሚገኙት በመሆናቸዉ መጠየቅ የሚችሉት ከሚች ድርሻ እንጂ በጣልቃ ገብ ከሚታወቀዉ ግማሽ ድርሻ ባለመሆኑ፤ የዚህ ቤት ግማሹ 50% የጣልቃ ገብ ድርሻ ሲሆን ቀሪዉ ግማሽ ድርሻ ላይ 25% ለሚች ወራሾች ለ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ድርሻ፣ ቀሪዉ 25% ድርሻ ደግሞ ለ1ኛ አመልካች ሊሆን ይገባል በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔን በመሻር፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

አመልካቾች በ21/10/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የሥር ፍ/ቤት ሚች ሁለት ሚስቶች ስላሏቸዉ ለክርክር ምክንያት የሆኑትን ንብረቶች ለሶስት እኩል ሊከፋፈሉ ይገባል በማለት ያሳለፈዉ ዉሳኔ የቤተሰብ ሕጉን የተከተለ አይደለም፤ የክፍፍል መርህ ሊሆን የሚገባዉ ሚች የንብረቶቹን ግማሽ ድርሻ እና ሁለቱ ሚስቶች ደግሞ ግማሽ ሊከፋፈሉ ይገባቸዋል፤ የሚች ድርሻ ከግማሽ ሊያንስ የሚችለዉ አንደኛዉ ተጋቢ ለንብረቱ መፈራት የተለየ አስተዋጽኦ ያደረገ ከሆነ ብቻ ነዉ፡፡ ለንብረቶቹ መፈራት አንደኛዋ ተጋቢ ንብረቷን በግል ጥረቷና በቀጥታ አስተዋጽኦ ማድረጓን ማስረዳት እስካልቻሉ ድረስ የንብረቱ ክፍፍል በሕጉ መሰረት ባል የሆነዉ ሚች ግማሽ ድርሻ ሆኖ ቀሪዉ ግማሽ ድርሻ ደግሞ ሁለቱ ሚስቶች እኩል የሚከፋፈሉት ይሆናል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ዉሳኔ ተሻሽሎ ከሚች እና ከተጠሪ ጋብቻ በፊት ከተፈራዉ የመኖሪያ ቤት ዉጭ ያለዉን ንብረት ግማሽ ድርሻ የሚች ወራሾች የሆኑት 2ኛ እና 3ኛ አመልካች፣ ቀሪዉ ግማሽ ድርሻ 1ኛ አመልካች እና ተጠሪ እኩል እንዲካፈሉ፣ ወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብታችን እንዲጠበቅልን በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል የንብረት ክፍፍል ድርሻቸዉን የወሰነበትን አግባብነት፣ ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት የካቲት 18 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ አመልካቾች በን/ስ/ላ ክ/ከተማ ዉስጥ የሚገኘዉን ቤት፣ መኪና እና በባንክ ያለዉን ገንዘብ እና በአዲስ ኢንተርናሽናል አ.ማ ያለዉን የአክስዮን ድረሻ በተመለከተ በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቅሬታ ቀርቦ ባልተሰማበት አሁን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ በኮ/ቀ/ክ/ከ ወረዳ 9 ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር የቤት ቁጥር B07 እና 08 የሆነዉ ንግድ ቤት በተመለከተ ቤቱ የተፈራዉ ሚች ከተጠሪ ጋር ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ትዳር መስርተን በአንድነት አብረን በምንኖርበት ሥፍራ በጋራ ያፈራነዉን ንብረትና በተጠሪም ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ነዉ፡፡ በመሆኑም ተጠሪ እና ሚች ይህን አከራካሪዉን ንብረት እኩል ድርሻ ያለን እንጂ አንዳችን ከአንዳችን የተለየ በአብላጫም ሆነ የአነሰ ድርሻ የሌለን መሆኑን በሕጉ የተረጋገጠ ነዉ፡፡ ስለሆነም 1ኛ አመልካች በስሜ የተመዘገበዉን ንብረት ከሚች ጋር የሚደርሳቸዉን ድርሻ እኩል ከሚካፈሉት በስተቀር ከተጠሪ ድርሻ ላይ ሊካፈሉ የሚችሉበት የህግ አግባብ ስለሌለ የአመልካቾች አቤቱታ የሕግ መሰረት የሌለዉ ስለሆነ ዉድቅ እንዲሆንልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካቾች በ5/8/2014 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካለቸዉ የህግ ደንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በን/ስ/ላ/ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ዉስጥ የሚገኘዉ የቤት ቁጥር አዲስ፣ የሰሌዳ ቁጥር 02-01-29047 አ.አ. አዉቶሞቢል መኪና፣ በተለያዩ ባንኮች አለ የተባለዉን ተቀማጭ ገንዘብ እና በአዲስ ኢንተርናሽናል አ.ማ አለ የተባለዉን የአክስዮን ድርሻ እና ትርፍ በተመለከተ አመልካቾች ባቀረቡት ቅሬታ እነዚህ ንብረቶች አስመልክቶ የክፍፍል ስርዓቱ መሆን ያለበት ሚች የንብረቶቹ ግማሽ ድርሻ ለሚች ወራሾች ለሆኑት ለ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የሚገባ ሲሆን፣ ቀሪዉ ግማሽ ድርሻ ደግሞ የሚች ሚስቶች ለሆኑት ለ1ኛ አመልካች እና ለተጠሪ ሆኖ ይህን ግማሽ ድርሻ እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን፣ ተጠሪ በበኩላቸዉ ባቀረቡት ክርክር የሥር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች እነዚህን ንብረቶች በተመለከተ ጭብጥ በመያዝ ግራ ቀኙን ባላከራከሩበት፣ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት እነዚህን ንብረቶች አስመልክቶ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት የወሰነ በመሆኑ አሁን ለዚህ ችሎት ሊያቀርቡ የሚችሉበት አግባብ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ አንጻር አመልካቾች የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር ያሳለፈዉን ዉሳኔ በመቃወም ቅሬታቸዉን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን፣ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር ባሳለፈዉ ዉሳኔ እነዚህን ንብረቶች አስመልክቶ ቅሬታ መቅረቡን የማያመለክትና እንደጭብጥ ተይዞ ዉሳኔ ያሳረፈበት መሆኑን አያሳይም፡፡ አመልካቾች እነዚህን ንብረቶች በተመለከተ የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም ቅሬታቸዉን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዉ ከሆነና ፍ/ቤቱ በዝምታ አልፏቸዉ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔን ያጸና እንደሆነ፣ አመልካቾች ከእነዚህ ንብረቶች አንጻር ቅሬታ ካላቸዉ በሕጉ በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ማቅረብ የሚገባቸዉ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 (1፣ ሀ) መሰረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሆን ነበረበት፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ በኮ/ቀ/ክ/ከ ወረዳ 9 ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር B07 እና 08 የሆነዉ ንግድ ቤት በተመለከተ ግራ ቀኙን በማከራከር ይህን የንግድ ቤት አስመልክቶ ብቻ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማሻሻል መወሰኑን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እነዚህን ንብረቶች በተመለከተ ግራ ቀኙን በማከራከር ጭብጥ በመመስረት ዉሳኔ መስጠቱን የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በን/ስ/ላ/ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ዉስጥ የሚገኘዉ የቤት ቁጥር አዲስ፣ የሰሌዳ ቁጥር 02-01-29047 አ.አ. አዉቶሞቢል መኪና፣ በተለያዩ ባንኮች አለ የተባለዉን ተቀማጭ ገንዘብ እና በአዲስ ኢንተርናሽናል አ.ማ አለ የተባለዉን የአክስዮን ድርሻ በተመለከተ ሕጉ በዘረጋዉ ሥርዓት መሰረት ቅሬታቸዉን ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ማቅረባቸዉን የሚያመለክት ነገር በሌለበት በቀጥታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች ባቀረቡት ቅሬታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ በኮ/ቀ/ክ/ከ ወረዳ 9 ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር B07 እና 08 የሆነዉ የንግድ ድርጅት ቤት በተመለከተ ባል (ሚች አቶ ሰይፉ መንግስቱ ግማሽ ድርሻ) ለሚች ወራሾች ለሆኑት ለአሁን 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች እና ሁለቱ ሚስቶች 1ኛ አመልካች እና ተጠሪ ደግሞ የቤቱን ግማሽ ድርሻ እኩል እንዲካፈሉ መወሰን ሲገባዉ፣ ተጠሪ ንብረቱን በማፍራት ረገድ የተለያ

አስተዋጽኦ ማድረጓን ባላስዳችበት፣ ተጠሪ ከባል ድርሻ በላይ የቤቱን ግማሽ ድርሻ እንዲትወስድ መወሰኑ የሕግ ድጋፍ የለዉም በማለት የተከራከሩ ሲሆን፤ ተጠሪ በበኩላቸዉ ይህን ንብረት ተጠሪ እና ሟች በትዳር እያለን በጋራ ጥረትና ድካም ያፈራነዉ በመሆኑ እኩል የመካፈል መብት ያለን ስለሆነ 1ኛ አመልካች መካፈል ያለባቸዉ ከሟች ድርሻ እንጂ ከተጠሪ ድርሻ የሚትካፈልበት አግባብ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ አንጻር በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ሲታይ 1ኛ አመልካች፣ ተጠሪ እና ሟች በትዳር አብረዉ እያሉ አከራካሪዉን የንግድ ቤት ማፍራታቸዉን እንጂ አንደኛዉ ተጋቢ በተሻለ ሁኔታ ንብረቱን ለማፍራት አስተዋጽኦ ማድረጋቸዉን በማስረጃ አለመረጋገጡን፣ ቤቱ በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን፣ 1ኛ አመልካች ባቀረቡት ክርክር ከንብረቱ 25% ወይም 1/4ኛ ድርሻ የሚገባቸዉ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡ እንዲሁም ተጠሪ ባቀረቡት ክርክር ይህን የንግድ ቤት ከሟች ጋር በትዳር እያለን በጋራ ያፈራነዉ የጋራ ሀብታችን ስለሆነ እኩል ሊካፈል ይገባል ከማለት ባለፈ ቤቱን ለማፍራት በተሻለ ሁኔታ አስተዋጽኦ ማድረጋቸዉን ገለጸዉ የአብላጫ ድርሻ ይገባኛል በማለት ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ መኖሩን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ አያሳይም፡፡

እንደሚታወቀዉ ባልና ሚስት በትዳራቸዉ ዉስጥ በጋራ ያፈሩትን ንብረት እኩል የመከፋፈል መብት ያላቸዉ መሆናቸዉን ከፌዴራሉ የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 62 (1)፣ 63 (1) እና 90 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚህ መሰረት ሟች አቶ ሰይፉ መንግስቱ እና ተጠሪ በኮ/ቀ/ክ/ከ ወረዳ 9 ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር የቤት ቁጥር B07 እና 08 የሆነዉ የንግድ ድርጅት ቤት በትዳር ዉስጥ እያሉ በጋራ ማፍራታቸዉን እንጂ አንደኛዉ ተጋቢ ንብረቱን በማፍራት ረገድ ከሌላኛዉ ተጋቢ በተሻለ ሁኔታ አስተዋጽኦ ማድረጉን ያስረዳበት ሁኔታ የሌላ በመሆኑ፣ ሟች እና ተጠሪ በዚህ ንብረት ላይ እኩል ድርሻ ከሚኖራቸዉ በስተቀር ተጠሪ የበለጠ ድርሻ የሚያገኙበት አግባብ መኖሩን የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ የሟችም ወራሾች ከተጠሪ የበለጠ ድርሻ የሚያገኙበት አግባብ አይኖርም፡፡ በሌላ በኩል 1ኛ አመልካች ከሥር ፍ/ቤቶች ጀምሮ እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ባቀረቡት ክርክር ከንግድ ቤቱ 25% ወይም 1/4ኛ ድርሻ እንደሚገባቸዉ በመከራከራቸዉ ባለፈ ከዚህ በላይ ድርሻ ይገባኛል በማለት ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ 1ኛ አመልካች ከዚህ ንብረት ይገባኛል ብለዉ ከጠየቁት ድርሻ በላይ የሚወሰንበት አግባብ አይኖርም ማለት ነዉ፡፡ በመሆኑም የሟች ወራሾች የሆኑት 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ከዚህ ንግድ ቤት የሟች አባታቸዉን ድርሻ 37.5%፣ ተጠሪ ደግሞ 37.5% ድርሻ ይገባቸዋል፤ እንዲሁም 1ኛ አመልካች ደግሞ ከንግድ ቤቱ 25% ወይም 1/4ኛ ድርሻ የሚገባቸዉ ይሆናል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች አከራካሪዉን የንግድ ድርጅት ቤት በተመለከተ በዚህ አግበብ የግራ ቀኞቸዉን የድርሻ መጠን መወሰን ሲገባቸዉ ከዚህ የሚቃረን የክፍፍል ዉሳኔ መስጠታቸዉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች አከራካሪዉንና በኮ/ቀ/ክ/ከ ወረዳ 9 ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር B07 እና 08 የሆነዉን የንግድ ድርጅት ቤት ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ አግባብ ግራ ቀኞቸዉ እንዲከፋፈሉ መወሰን ሲገባቸዉ የሟች ወራሾችን እና የተጠሪን ድርሻ በተመለከተ ያሳለፉት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

# ዉሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ.ቁ97386 በ3/4/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.208128 በ6/2/2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.186518 መጋቢት 30 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የሥር ፍ/ቤቶች በኮ/ቀ/ክ/ከ ወረዳ 9 ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር B07 እና 08 የሆነዉን የንግድ ድርጅት ቤት በተመለከተ የሚች ወራሾችን ድርሻ እና የተጠሪን ድርሻ አስመልክቶ ያሳለፉት የዉሳኔ ክፍፍል ተሽሯል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤቶች በኮ/ቀ/ክ/ከ ወረዳ 9 ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር B07 እና 08 የሆነዉ የንግድ ድርጅት ቤት በተመለከተ የ1ኛ አመልካች ድርሻ 25% ወይም 1/4ኛ ነዉ በማለት ያሳለፉት ዉሳኔ አልተነካም ጸንቷል፡፡
4. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሌሎች ንብረቶችን በተመለከተ ያሳለፉት የዉሳኔ ክፍል አልተነካም ጸንቷል፡፡
5. አከራካሪዉና በኮ/ቀ/ክ/ከ ወረዳ 9 ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር B07 እና 08 የሆነዉ የንግድ ድርጅት ቤት በተመለከተ የሚች ወራሾች 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ከቤቱ 37.5% ድርሻ፣ ተጠሪ ከዚህ ቤት 37.5% ድርሻ እንዲሁም 1ኛ አመልካች ከዚህ ቤት 25% ድርሻ ሊከፋፈሉ ይገባል፡፡ በዚህ አግባብ ግራ ቀኞቸዉ ቤቱን ከተቻለ በዓይነት እንዲከፋፈሉት፣ ካልተቻለ በስምምነት እንዲከፋፈሉት፣ ይህም ካልተቻ በስምምነት ሸጠዉ እንዲከፋፈሉት፣ ይህም ካልተቻለ ቤቱን በጨረታ ሸጠዉ እንዲከፋፈሉት ብለናል፡፡
6. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
7. ግራ ቀኞቸዉ የሰበር ክርክሩ ያደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
8. የመ.ቁ.97386 የሆነዉ መዝገብ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ን/ስ/ላ/ ምድብ ችሎት ይመለስ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

**አ/መ** **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

*ማ ሰታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ አንጂ*
*ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*